# ከእግዚአብሔር ፍቅር

" ... እኔ የሚረባህን ነገር የማስተምርህ በምትሄድባትም መንገድ የምመራህ አምላክህ እግዚአብሔር ነኝ።" (ኢሳ 48 ፥ 17)
God's Love, P.O.Box 6734 , Lee's Summit, MO, 64064. አዘጋጅ መላኩ ትዕዛዙ E-mail – hello@ethiogodslove.org

www.ethioGodslove.org ኅዳር 1997 November 2004

ልጆችሽም ሁሉ ከእግዚአብሔር የተማሩ ይሆናሉ፥የልጆችሽም ሰላም ብዙ ይሆናል (ትንቢተ ኢሳይያስ 54፥13)

## ጥቃቅን ቀበሮች

"ወይናችን፡አብቦአልና፡የወይናችንን፡ቦታ የሚያጠፉትን፡ቀበሮች፥ጥቃቅኑን፡ቀበሮች፡አጥምዱችሁ፡ያዙልን።"
(መኃልየ መኃልይ ዘሰሎሞን 2፥15)

በሰው ግምት ጥቃቅን የምንላቸው በእግዚአብሔር ፊት ግን በቀላሉ የማይ ወሰዱ፥ብዙ ነገሮች መኖራቸውን፥ በመ ጽሐፍ ቅዱሳችን በሰፊው እናያለን። እንዲያውም ከሁሉ የከፋውን ውድቀት በሰው ላይ ያመጣውን ጥፋት በጥሬው ስንመለከት፥ ጥቃቅን ልንለው የሚቻል ይመስላል።በኤድን ገነት ከሞሉት ዛፎች የአንዱን ፍሬ መብላት ፥ ፊት ለፊት ሲታይ ትልቅ ላይመስል ይችላል። መሠ ረቱ ግን፥ በእግዚአብሔር ላይ አመፃና ኃጢአትም በመሆኑ፥ውጤቱ ለትውልድ የሚተላለፍ ውድቀት ሆነ።

ዛሬም ቢሆን ያው ነው። በየዕለቱ ኑሮ ሰዎች በቸልታ የሚለማመዱአቸውን ጥቃቅን ኃጢአቶች፡- ጌታ በቀላሉ ሊመ ለከት አይችልም። ስለዚህ በንስሐ ያል ተወገዱ ጥቃቅን መሳይ ኃጢአቶች፥በአ ማኞች ሕይወት ውስጥ ፍሬ እንዳይታይ ና ፀሎታቸው እንዳይመለስ በመከልከል የሴይጣን መሣሪያ ሆነው ይሠራሉ። "በልቤስ፡በደልን፡አይቼ፡ብሆን፡ጌታ፡አይ ሰማኝም፡ነበር።" ተብሎ በመዝ/ ዳዊት 66፥18 እንደ ተጻፈው።

የሚከተሉት፥ ጥቃቅን ቀበሮዎች ሆነው የክርስቲያኖችን ሕይወት ከመለምለምና ከማፍራት የሚከለክሉ ማነቆዎች ናቸው

✗ **ትዕቢት**፡- ብዙ ክርስቲያኖች ይህ ችግር እንዳለብን አናምንም። ምክንያቱ ም ትዕቢት ለባለቤቱ ጎልቶ ስለማይታ ይና ሳያስቡበትም ስለሚሆን ነው።

"እግዚአብሔርን፡መፍራት፡ክፋትን ይጠ ላል፥ትዕቢትንና፡እብሪትን፡ክፉንም፡ መን ገድ፡ጠማማውንም፡አፍ፡እጠላለሁ።"
(መጽሐፈ ምሳሌ 8፥13)

✗ **ማጋነን**፡- ይህም ከትዕቢት ጋር ይዛ መዳል። ምንም እንኳን የዋኅና የማይጐ ዳ ቢመስልም፥ ከውሸት ጋር የተያያዘ በመሆኑ፡ ኃጢአት ነው።

✗ **ተስፋ ቆራጭ (አስቆራጭነት)**፡- ይህ ደግሞ ቶሎ ካልተነቃበት ክፋቱ ከማን ኛውም ጠላት የሚያንስ፥ በክፉ ጊዜዎች የሚጠናወት በሽታ ነው።

✗ **ዓለምን መምሰል**፡- ከሰዎች ሥርዓት ና ከዚህ ዓለም ፍላጎት ጋር ለመግባባት መሞከር ከንቱ ልፋት ነው። ከዚህ የተነ ሣ መንፈሳዊ ኃይላቸውን ያስሰረቁ ብዙ ክርስቲያኖችና ቤተ ክርስቲያኖች ታይ ተዋል።"የእግዚአብሔር ፈቃድ እርሱም በጎና ደስ የሚያሰኝ፡ ፍጹምም የሆነው ነገር ምን እንደ ሆነ ፈትናችሁ ታውቁ ዘንድ በልባችሁ መታደስ ተለወጡ እን ጂ ይህን ዓለም አትምሰሉ። (ሮሜ 12፥2)

✗ **ፍርሐትና ጥርጣሬ**፡- ይህ ክፉ ነገር ብዙዎችን ከእግዚአብሔር መንግሥት እያራቀ በእስራት አኑሮአል። የዕምነት ተቃራኒ ስለ ሆነ፥ በሰዎች ድካም ወቅት የሚያጠቃ ጨካኝ ጠላት ነው። ፍርሐት ም በብዙ መልኩ ይገለጣል። ለምሳሌ ይ ጠሉኛል ወይም ይንቁኛል ብሎ መጠራ ጠር አንዱ ነው። ፍርሐትና ጥርጥር ለመንፈስ ቅዱስ የሚያመች፥ ሴይጣናዊ ባሕሪያት ናቸው።

✗ **ጭንቀት**፡-ነገሮች ሲበላሹ የሚከሰት ስጋዊ ስሜት ነው። በዕውነቱ ግን ያው ያለማመን ኃጢአት ነው።

✗ **ተበዳይነትና በቀል** ፡- ይህ ተጎጻሁ በምንልበት ጊዜ የሚገለጽብን ተፈጥሮአ ዊ ስሜት ነው። ሥጋዊም ባሕሪይ ስለ ሆነ የመንፈስ ቅዱስ ተቃዋሚ ነው። "እንደ ሥጋ ፈቃድ ብትኖሩ ትሞቱ ዘን ድ አላችሁና፡ በመንፈስ ግን የሰውነትን ሥራ ብትገድሉ በሕይወት ትኖራላችሁ"
(ወደ ሮሜ ሰዎች 8፥13)

✗ **ሐሜትና ወሬ አመላላሽነት**፡- ሁሉን ም የሚጎዳ፥በቶሎ ካልተቀረጠ በእግዚአ ብሔር ቤት ውስጥ አንድነትን የሚፃረር አጋንንታዊ ባሕሪይ ነው።

✗ **አለመታገሥ**፡- ወደ ቁጣና ወደ ጥፋ ት ስለሚያደርስ ጊዜ ሳንወስድ ማስወገ ድ የሚገባን የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ ተቃ ራኒ ነው። "ትዕግሥትም ምንም የሚጐ ድላችሁ ሳይኖር ፍጹማንና ምሉዓን ት ሆኑ ዘንድ ሥራውን ይፈጽም።"
(ያዕቆብ 1፥4)

✗ **ማጉረምረም**፡- ይህ ደግሞ እንደ ቀላ ል የሚታይ ጉዳትም እንዳለው የማይታ ሰብ ልማድ ነው። ሆኖም እግዚአብሔር ን እጅግ የሚያስቆጣ ነገር ነው።"ሕዝቡ ም ክፉ ሆነው በእግዚአብሔር ላይ አጉ ረመረሙ፥እግዚአብሔርም ሰምቶ ተቆጣ፡ የእግዚአብሔርም እሳት በመካከላቸው ነደደች፥ የሰፈሩንም ዳር በላች።"
(ዘኍልቍ 11፥1)

✗ **ፉክክር፥ቅናትና ምቀኝነት**፡- መንፈ ሳዊ ብስለትና ትሕትና በጐደላቸው ሰዎ ች ውስጥ የሚሠሩ የፍቅርና የሰላም ፀር ናቸው። እንዲህ ያሉ ሰዎች ጥፋታቸው አይታወቃቸውም። ይህም ሴይጣናዊ ባሕሪይ ነው።

✗ **ክብር ፈላጊነት፥ተቀያሚነት**፡-እነዚ ህም በሰው ልብ ተደብቀው ባለቤቱን ሰላምና ደስታ የሚነፍጉ፥ማሕበራዊ ኑሮ ንም የሚያውኩ ባሕሪያት ናቸው።

እንግዲህ ወገኖች ሆይ፡- እነዚህና እነ ዚህንም የመሳሰሉት በየዕለቱ ኑሮ የሚገ ለጡ በርካታ ነገሮች ናቸው፥ በዘልማድ ጥቃቅን ተብለው የሚወሰዱት። ነገር ግን ቤተሰብን ፥ ቤተ ክርስቲያንን ሆነ ማኅበራዊ ኑሮን ለማተራመስ የሴይጣን ብርቱ መሣሪያ ናቸው። የእግዚአብሔር ሰዎች ሴይጣንን በእንባሣነቱ ሲያሳድዱ ት እርሱ ግን በእነዚህ "ጥቃቅን ቀበሮዎች በመጠቀም፥ከውስጥ ሆኖ፥ክፋቱን ይፈ ጽማል፤ ጌታ ይገስጻው።

ድል ለመንሣት የሚተጉ ሁሉ ግን፥ እነዚህን ፀረ ጽድቅና ፀረ ቅድስና ባሕሪ ያት አሸንፈው የተስፋውን ሙላት ለመ ቀዳጀት ይተጋሉ።

"ድል የነሣው በአምላኬ መቅደስ ዓምድ እንዲሆን አደርገዋለሁ፥ወደ ፊትም ከዚ ያ ከቶ አይወጣም፡ የአምላኬን ስምና የአምላኬን ከተማ ስም፥ ... አዲሲቱን ኢየሩሳሌምን፥አዲሱንም ስሜን በእርሱ ላይ እጽፋለሁ።" (የዮሐንስ ራዕይ 3፥12)

ወገኖቼ፥ ብዙ ተስፋ ያለን፥ ብዙም ምርኮ የሚጠብቀን ሕዝብ ነን፤ እግዚአ ብሔር ይመስገን።የሚጠብቀንን የክብር ተስፋ እያሰብን የእግዚአብሔርን መንግ ሥት፥ጽድቁንና ቅድስናውን በሕይወታ ችን ለማከናወን ልንጨክን በቂ ምክንያ ት ያለን ሕዝብ ነን። የተጠራነው ክርስ ቶስን ለመምሰል ታላቅ ክብር ነው፤ ክብ ር ለስሙ ይሁን። ለዚህ ታላቅ ዘላለማዊ ክብር የጠራን ፥ እንቀደስበትም ዘንድ ቃሉን የሰጠን የእስራኤል ቅዱስ ጌታ ይባረክ። አሜን።

## የአባት ደብዳቤ

ይህ ዕውነተኛ የአባትህ ደብዳቤ ነው። ቃሉም ዕውነተኛና የታመነ ነው። ከፈቀ ድህለት ሕይወትህን ለመልካም ይለውጣ ል። በሰማይ ከሚኖረው ከሚውድህ አባ ትህ ልብ የመነጩ ቃላት ስለ ሆኑ የልብ ህን ዓይኖች ያበራሉ። ዕድሜህን በሙሉ ፈልገህ ያላገኘኸውን ዕውነተኛውን አባ ትህን ታገኘዋለህ። ብታውቅም ባታውቅ ም እግዚአብሔር አባትህ ነው ። ይህ የእግዚአብሔር ፍቅር ደብዳቤ ነው።

አባትህ እግዚአብሔር እዲህ ይልሃል።

ልጄ ሆይ፡-

አንተ አታውቀኝ ይሆናል። እኔ ግን ስላ ንተ ሁሉን አውቃለሁ። አካሄድህም በሙሉ በፊቴ የተገለጹ ናቸው።
መዝ/ ዳዊት 139፥1-3

የራስህን ጸጉሮች ሁሉ እንኳ በቁጥራቸ ው አውቃቸዋለሁ። ማቴዎስ 10፥30

ምክንያቱም ከመጀመሪያውም የፈጠር ኹህ በክቡር አምሳሌ ስለ ሆነ ነው።
ኦሪት ዘፍጥረት 1፥27

የምትኖረውና የምትንቀሳቀሰው በእኔ ነው። ሐዋሪያት ሥራ 17፥28

ገና በሆድ ሳልሠራህ አውቄሃለሁ፥ከማኅ ፀንም ሳትወጣ ቀድሼሃለሁ፥
ትንቢተ ኤርምያስ 1፥5

ልጄ እንድትሆን የመረጥሁህ ገና የፍጥ ረትን ዕቅድ ሳላወጣ ነበር።
ኤፌሶን 1፥11-12

አንተ፥በአጋጣሚ የተገኘህ አይደለህም። የአንተ ነገር በሙሉ በእኔ ዘንድ የታወቀ ነው። መዝ/ 139፥1-3

የትውልድህን ዘመንና ሐገር ሁሉ የወሰንሁት እኔ ነኝ። የሐ/ሥራ 17፥26-27

ግሩምና ድንቅ አድርጌ የፈጠርሁህ፥በእናትህም ማኅፀን የሰወርሁህ እኮ እኔ ነኝ መዝ/ 139፥13-14

ልጄ:- "ከማሕፀን ጀምሮ ደግፌሃለሁ፥ ከእናትህም ሆድ ጀምሮ መሸሸጊያህ ነኝ: መዝ/ 71፥5-6

አንዳንዶች በፈቃዴ ሳይኖሩ አባታችን ይሉኛል። ዮሐንስ ወንጌል 8፥39-45

እኔ ግን አንተን ያፈቀርሁበት ፍቅር ታላቅ ነው። ልጄ እንድትሆን ስለፈጠርሁህ ብቻ እንዲያው እወድሃለሁ። 1የዮሐንስ መልክት 3፥1

እኔ የማደርግልህና የምሰጥህ ከሥጋ አባትህ እጅግ አብልጬ ነው። የማቴዎስ ወንጌል 7፥11

እኔ ፍጹም የሆንሁ ሰማያዊ አባትህ ነኝ: የማቴዎስ ወንጌል 5፥48

ብታስታውልም፥ ባታሰታውልም በጎ ስጦታ ሁሉ ፍጹምም በረከት ሁሉ ከእኔ ናቸው። የያዕቆብ መልክት 1፥17

አስቀድመህ ጽድቄንና መንግሥቴን ፈልግ እንጂ፥ የሚያስፈልግህን ሁሉ እጨምርልሃለሁ ብዬ በቃሌ አልነገርሁህምን? የማቴዎስ ወንጌል 6፥31-33

ለልጆቼ የማስባትን አሳብ እኔ አውቃለሁ: ፍጻሜና ተስፋ እሰጣችሁ ዘንድ የሰላም አሳብ ነው እንጂ የክፉ ነገር አይደለም። ትንቢተ ኤርምያስ 29፥11

አሁንም ወደ እኔ እንድትመለስ የማባብልህና በቸርነት የምስብህ ስለምወድህ ነው። ትንቢተ ኤርምያስ 31፥3

ለአንተ ያለኝን ሃሳብ ብትረዳ ኖሮ በፈቃድህ ወደ እኔ በሮጥህ ነበር። መዝሙረ ዳዊት 139፥17

በአንተ ከማደርገውም በጎነት አልመለስም። ትንቢተ ኤርምያስ 32፥40

አሁንም ቃሌን በዕውነት ብትሰማ ኪዳኔንም ብትጠብቅ፥ ምድር ሁሉ የእኔ ናት ና፥ከአሕዛብ ሁሉ የተመረጠ ርስት ትሆነኛለህ:... ኦሪት ዘጸአት 19፥5

ልጄ:- በዕምነት ወደ እኔ ብትጮኽ፥ ታላቅና ኃይለኛ ነገር ላሳይህ መውደዴን ምን ነው ብትረዳ? ት/ ኤርምያስ 33፥3

ለመሆኑ እግዚአብሔር አይታወቅም ብለህ ተስፋ የምትቁርጠው ለምንድን ነው? "በልብህ ሁሉ፥ በነፍስህም ሁሉ የፈለግኸው እንደ ሆነ ታገኘዋለህ" ብዬ አልነገርሁህምን? ኦሪት ዘዳግም 4፥29

አንተ ብቻ "በእግዚአብሔር ታመን፥መልካምንም አድርግ፥በምድርም ተቀመጥ ታምነህም ተሰማራ። (እንጂ) በእግዚአብሔር ደስ ይበልህ፥ የልብህንም መሻት ይሰጥሃል።" መዝሙረ ዳዊት 37፥3-4

ምክንያቱም "ስለ በጎ ፈቃዱ መፈለግንም ማድረግንም በእናንተ የሚሠራ እግዚአብሔር ነውና።" ፊልጵስዩስ 2፥13

የእኔ ፍላጎት እኮ ከሰዎች መካከል ለመኖርና፥ አምላካቸው ሆኜ፥ ዕንባዎችን ሁሉ ከዓይኖቻቸው ማበስ ነው። የዮሐንስ ራዕይ 22፥3

በመጨረሻም:- ሁሉም ነገር እንደ ፈቃዴ ይሆናል። ከዚያም በኋላ:- "... መርገም ከቶ አይሆንም። የእግዚአብሔርና የበጉም ዙፋን በእርስዋ ውስጥ ይሆናል፥ ባርያዎቹም ያመልኩታል፥ፊቱንም ያያሉ፥ስሙም በግምባሮቻቸው ይሆናል።" የዮሐንስ ራዕይ 22፥3-4

ልጄ ሆይ:- እኔ አንተን የምወደው ከልጄ ከእየሱስ እኩል መሆኑን ከቃሌ አንብበህ ተረድተሃልን? የዮሐንስ ወንጌል 17፥23

ልጄስ እየሱስ የፍቅሬ መግለጫ መሆኑን አውቀህ አምነሃል? የዮሐንስ ወንጌል 17፥26

ለመሆኑ ልጄ እየሱስ:- የክብሬ ነጸብራቅና የባሕሪዬ ምሳሌ መሆኑ ይገባሃል? ዕብራውያን 1፥3

አማኑኤል: ልጄን ወደ ምድር የላክሁት እኔ ከአንተ ጋር ከሆንሁ ማንም ሊቃወምህ እንዳይችል ነው። ሮሜ 8፥31

እየሱስ የሞተው አንተን ከእኔ ጋር ለማስታረቅና በእርሱ ምክንያት በደልህ ሁሉ እንዳይቆጠርብህ ነው። 2 ቆሮንቶስ 5፥18-19

ልጄን እየሱስን ለመስቀል ሥቃይና ሞት አሳልፌ መስጠቴ ለአንተ ያለኝን ፍቅር መጠን የሚገልጽ ነው። 1ዮሐንስ 4፥10

ከእኔ ጋር ሰላምን የሚፈልግ ሰው ሁሉ ማድረግ ያለበት ግዴታ ይህ ነው። "ትዕዛዜቱም ይህች ናት፥በልጁ በእየሱስ ክርስቶስ ስም እናምን ዘንድ ፥ ትዕዛዝንም እንደ ሰጠን እርስ በርሳችን እንዋደድ ዘንድ።" 1ኛ የዮሐንስ መልዕክት 3፥23

እንዲህም ከታዘዝኸኝና እግዚአብሔርን በመመፍራት ከኖርህ:- ማንም፥ ምንም ከፍቅሬ ሊለይህ አይችልም። ሮሜ 8፥39

እንግዲህ ልጄ ሆይ:- ታግሠህ ይህን ሁሉ እንድታነብብ ረድቼሃለሁ። አሁን ይህን እጠይቅሃለሁ። ከዚህ በፊት ሕይወትህን ለሞተልህ ልጄ ለየሱስ ካልሰጠህና፥ ዛሬ ብትሞት መንግሥተ ሰማይ መግባትህን ርግጠኛ ካልሆንህ፥ አሁን ንስሐ ግባ። አሁን ተንበርክከህ የሚከተለውን ፀሎት ፀልይ። በሰማይም ስለ አንተ ደስታ ይሆናል። የሉቃስ ወንጌል 15 ፥ 7

ወድ ልጄ:- ልቆጣህ ሳይሆን በፍቅሬ ልቀበልህ በተዘረጉ እጆች እጠባበቅሃለሁ የሉቃስ ወንጌል 15፥11-32



ሁሉን የምገዛ፥ሁሉን የምችል፥ የምወድህ: ሕያው እግዚአብሔር አባትህ።

## የደኅንነት ፀሎት:-

ጌታ እግዚአብሔር ሆይ፥ ወደ አባትነትህ ፍቅር መንግሥት ለመግባት ልጅህን እየሱስን ጌታዬ ብዬ እቀበለዋለሁ። ከዛሬ ጀምሮ በምትገልጽልኝ ፈቃድህ መሠረት እኖራለሁ። አባቴ ሆይ፥ልጅህ አድርገህ ስለ ተቀበልኸኝ አመሰግንሃለሁ በቀረው ዕድሜዬ አንተን በመፍራት እኖራለሁና ርዳኝ። አሜን።

ውድ ወንድሜና እኅቴ:- ይህንን ፀሎት በዕውነት አምነህ/ሽ ከፀለይህ/ሽ፥ መለኮታዊ ሚስጢር በሆነ አኳኋን፥ መንፈስ ቅዱስ ወደ ልብህ ይገባል። እርሱም 1ኛ የመንግሥተ ሰማያት ወራሽነትህ ማኅተም ነው። 2ኛ ኃጢአትን አሸንፎ ለመኖር የሚረዳና የሚመራ ጸጋ ነው። 3ኛ እግዚአብሔርን ለማገልገልና ለማምለክ የሚያግዝ የጽድቅ ቀባት ሆኖ በሕይወትህ ውስጥ ይኖራል። እየሱስን በዕውነትና በንስሐ የተቀበለ ሰው መንፈስ ቅዱስ በሕይወቱ ውስጥ መኖሩን ፥ ወዲያውኑ ወይም ቃሉን መረዳት ሲጀምር ይረዳል

ማሳሰቢያ:- ሕይወቱን በእየሱስ ዕምነት ለእግዚአብሔር ያስረከበ ሰው ወዲያው ለሰዎችም፥ለሴይጣንም፥ለእግዚአብሔርም መናገር አለበት። ለሰዎች፥ስለ ምስክርነት፥ ለሴይጣን፥ ተስፋ እንዲቆርጥ፥ ለእግዚአብሔርና ለመላዕክቱ፥ በእርሱ ላለማፈራችንን ለመግለጥ ነው።

የዚህ ጽሑፍ አዘጋጅ ጌታዬንና አዳኜን፥ እየሱስ ክርስቶስን በተቀበልሁበት ጊዜ እንዲህ የመከረኝ ሰው ስላልነበረ፥ ጌታ መንፈስ ቅዱስ ሊያጸናኝ ሲል ልክ እንደዚህ ነበር ያለማመደኝ። በከሃዲ የአብዮት ነጎደኞቹና በእስላሞች ፊት፥ በታላቅ ድፍረት፥ እየሱስ ጌታዬ ነው እያልሁ እንድመሰክ ያደርገኝ ነበር። እነርሱም "ወይ ጉድ! ልጁ አበደ ወይስ ጴንጤ ሆነ?" ይሉ ነበር። ሰው ሁሉ መዳኔን በቶሎ አወቀ። በዚህም ምክንያት፥የተጠቀምሁት፥ሊያሰልሙኝ ያስቸግሩኝ የነበሩት አረቦቹ ከዚያ በኋላ ሊሰብኩኝ ወደ እኔ አልመጡም። ክብር ለጌታ ለመንፈስ ቅዱስ ይሁን። አሜን። ስለዚህ አንተም እንዲሁ አድርግ። ትጠቀማለህ። እግዚአብሔርም ይከብርብሃል።

ወአውሥአ:እግዚእ:ኢየሱስ:ወይቤሎ:አማን:አማን:እብለከ:ዘኢ.ተወለደ:ዳግመ:ኢይክል:ርእዮታ:ለመንግሥተ:እግዚአብሔር።
ወንጌል:ዮሐንስ: ፫፥፫

ኢየሱስም መለሰ:- እውነት እውነት እልሃለሁ፥ ሰው ዳግመኛ ካልተወለደ በቀር የእግዚአብሔርን መንግሥት ሊያይ አይችልም አለው:
የዮሐንስ ወንጌል 3፥3

*********

አገልግሎታችንን እንድትደግፉ ጌታ ቢያሳስባችሁ ወይም የአድራሻ ለውጥ ብታደርጉ በሚከተለው አድራሻ ጻፉልን።

God's Love
P.O.Box 6734
Lee's Summit, MO 64064
USA ወይም በኢ- ደብዳቤ
hello@ethiogodslove.org

የድር ገጻችንን ስትጎበኙ፥የእንግዶች መዝገባችንን ከፍታችሁ ማስታወሻ አስፍሩልን።
ጌታ ይባርካችሁ።

www.ethiogodslove.org
Please sign our gust book

እየሱስ ጌታ ነው።
ጌታ ይባርካችሁ።